# ጥናት አንድ 2ኛ ቆሮ 1፡1-11 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ስለ ቆሮንቶስ ቤተ ክርስትያን አስቀድሞ ወደ አዕምሮዬ የሚመጣልኝ ነገር ርኩሰቷ፣ መለያየት፣ ቅናት፣ ክርክርና የመሳሰሉት ነገሮች ናቸው፡፡ በዚህ ክፍል ይህች ቤተ ክርስትያን ‹‹የእግዚአብሄር ቤተ ክርስትያን›› በመባል ተጠርታለች፡፡ ቤተ ክርስትያን በምንም ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ብትሆንም የእግዚአብሄር ንብረት መሆኗ እንደማይቀየር እንማራለን፡፡
2. የርህራሄ አባት፣ የመጽናናት ሁሉ አምላክና፣ የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት የሚሉት ናቸው፡፡ የርህራሄ አምላክ ሲል የሚገባኝ ልክ አባት የነገሮች መገኛና ምንጭ እንደሆነ፤ እንዲሁም እግዚአብሄር የርህራሄ ምንጭ፣ መነሻና መጀመሪያ ነው ለማለት ይመስለኛል፡፡
3. እግዚአብሄር አማኞችን በመከራቸው ሁሉ ያጽናናቸዋል፤ መጽናናት አስቀድሞ ከእግዚአብሄር የተቀበለ ሰው ሁሉ ሌሎችን ማለትም በመከራ ውስጥ ያሉትን እርሱ በእግዚአብሄር በተጽናናበት መጽናናት የማጽናናት ሃላፊነት አለበት፡፡ በዚህ ቁጥር ላይ እንደምናየው አማኝ መከራ እንደሚያገኘው ብቻ ሳይሆን፤ የሚያልፍበት መከራ ለከንቱ ሳይሆን ዓላማ ያለው መሆኑንም እናነባለን፡፡
4. ጳውሎስ ያተኮረባቸው ሁለት ቃላት ‹‹መከራ›› እና ‹‹መጽናናት›› የሚሉት ናቸው፡፡ ይህ አነጋገሩ ሊያስረዳን የሚችለው ነገር ቢኖር እነጳውሎስ የገጠማቸው መከራ ለሌሎች መዳንና መጽናናት እስከሆነ ድረስ በደስታ የሚቀበሉት ነገር እንደሆነ ያሳየናል፡፡
5. እርግጠኛ ሆኖ የሚናገረው ነገር የቆሮንቶስ ሰዎች በነጳውሎስ መከራ እንደተካፈሉ ሁሉ በመጽናናታቸውም እንደሚካፈሉ ነው፡፡ ከዚህ የምረዳው ለጌታ ብሎ መከራን የሚቀበል ሰው ቁ4 ላይ ‹‹በመከራችን ሁሉ ያጽናናናል›› እንደተባለ ሁሉ እግዚአብሄር የመጽናናት ቀን እንደሚያመያለት አያለሁ፡፡
6. መከራቸው በህይወት ለመኖር እንኳን ተስፋ እስኪቆርጡ ያደረጋቸው ነው፣ ከአቅማቸው በላይ የሆነ መከራ ነበረ፣ ጽኑ የሆነ መከራ ነበረ፣ የሞት ፍርድ እንደተፈረደባቸው ይሰማቸው ነበረ፡፡ ስለደረሰባቸው መከራ የቆሮንቶስ ሰዎች እንዲያውቁ የፈለገው እኔ እንደሚመስለኝ እግዚአብሄር ከዚህ ዓይነቱ መከራ እነጳውሎስን ካዳናቸው እነርሱም በሚገጥማቸው መከራ ሊያድናቸው እንደሚችል እንዲረዱና እምነታቸውን በእርሱ ላይ እንዲያደርጉ ይመስለኛል፡፡
7. በእስያ ላይ ባዳናቸው ማዳን ብቻ የማይወሰን መሆኑን የምናየው በቁ10 ላይ በሃላፊ ጊዜ፣ በአሁን ጊዜና፣ በመጪ ጊዜ አድርጎ ጳውሎስ የእግዚአብሄርን ማዳን ተናግሮናልና ነው፡፡ በመከራችን ቅዱሳን የሚኖራቸው አስተዋጽዖ በጸሎት መደገፍ ሲሆን በዚያም መንገድ እግዚአብሄር ለሚሰጠው ድል ብዙ ምስጋናን ከቅዱሳኑ ሁሉ ያገኛል ማለት ነው፡፡
8. ይህ ሁሉ መከራ የደረሰባቸው ምክንያት ቁ9 እንደሚነግረን ሙታንን በሚያስነሳ በእግዚአብሄር እንጂ በራሳቸው እንዳይታመኑ ነው፡፡ ይህ የሚያስተምረኝ እግዚአብሄር ወደ ህይወቴ የሚልከው ማናቸውም ነገር ለእኔ መሰሪያና ማደጊያ እንጂ ለጥፋቴ እንዳልሆነ እማራለሁ፡፡

# ጥናት ሁለት 2ኛ ቆሮ 1፡12-24 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በነዚህ ቁጥሮች የምናየው ጳውሎስ የቆሮንቶስ ቅዱሳንን እንደሚጎበኛቸው ዕቅድ እንዳለው አስቀድሞ እንደነገራቸው፤ ዕቅዱን ግን ተግባራዊ ለማድረግ ባለመቻሉ አንዳንዶች ከነሱ መሃል የጳውሎስን ባህርይ በተለያየ መንገድ ሲነቅፉ፤ በተለይም በሁለት አፍ እንደሚናገር ማለትም ውሸት እንደሚቀላቅል አድርገው መናገራቸውን ሰምቶ ምላሽ ሲሰጣቸው ነው የምንመለከተው፡፡
2. የነጳውሎስ ትምክህት በዓለም ዘንድና በቅዱሳን ዘንድ ባላቸው ግንኙነት ከእግዚአብሄር በሆነ ቅድስናና ቅንነት መኖራቸው ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች ትምክህታቸው በ1ኛ ቆሮ 1፡31 ላይ በተጻፈው መሰረት የሚመካ በእግዚአብሄር ይመካ እንደሚል ቅድስናቸውም ሆነ ቅንነታቸው ከእግዚአብሄር ያገኙት እንደሆነ በዚያው ቁጥር ላይ ያሰፈሩት ስለሆነ ትምክህታቸው በማን እንደሆነ የሚያጠራጥር ነገር አልተውም፡፡
3. ከነዚህ ሁለት ክፍሎች የምንረዳው ነገር፤ ጌታ እስኪመጣ ድረስ የሰዎችን ማንነትም ሆነ ማናቸውንም ነገር ምንም ያህል ያወቅንና የተረዳን ቢመስለን እንኳን እውቀታችን በከፊል እንደሆነ፤ ነገር ግን ጌታ ሲመጣ ይህ በከፊል የሆነው እውቀት ተሸሮ ሙሉ ለሙሉ እንደምናውቅ ያስረዱናል፡፡ ችግሩን ያስከተለው ቅዱሳኑ የልቡን ሃሳብ ሁሉ እንደሚያውቁ አድርገው መናገራቸው ሲሆን፤ ነገር ግን የልቡ ሃሳብ እነርሱ እንዳሰቡት እንዳልሆነ ነው ሊያስረዳቸው የሚሞክረው፡፡
4. የጳውሎስ የልብ ፍላጎት የቆሮንቶስ ሰዎች በእጥፍ እንዲጠቀሙ እንደነበረ በቁ15 ላይ እናነባለን፡፡ እነርሱ ግን እቅዱን የተመለከቱት በመጀመሪያ ደረጃ በሚገባ ሳያስብበት እንዳደረገውና በተጨማሪም እንደአለማዊ ልማድ ማለትም እውነትና ውሸት እንደሚቀላቅል አድርገው ነው የሚናገሩት፡፡
5. በማቴ 5፡17 ላየ ኢየሱስ አዎአችን አዎ፣ አይደለማችን ደግሞ አይደለም እንዲሆን ያዘዘውን ትዕዛዝ ጳውሎስና ጓደኞቹ በተግባር ላይ እያዋሉ እንደሆነ ነው በዚህ ክፍል የምንረዳው፡፡ እነጳውሎስ ንግግራቸውን የሚያነጻጽሩት ከእግዚአብሄር ታማኝነት ጋራ ነው፡፡
6. ጓደኞቹ የሰበኩላቸው የእግዚአብሄር ልጅ የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን ነው፡፡ ‹‹አዎን›› እና ‹‹አይደለም›› የሚሉት አነጋገሮች እኔ እንደምረዳው እውነትና፤ ውሸት የሚለውን ሃሳብ ያዘሉ ናቸው፤ ማለትም የሰበኩላቸው ኢየሱስ አንዳንዱ እውነት አንዳንዱ ደግሞ ውሸት ሳይሆን፤ ስለእርሱ የተነገረው ነገር ሁሉ እውነት ነው ማለት ነው፡፡
7. እግዚአብሄር ጸንተን እንድንቆም ያደርጋል፣ ቀብቶናል፣ የእርሱ ለመሆናችን ማህተሙን አትሞብናል፣ የመንፈሱን ዋስትና በልባችን አኑሯል፡፡ የእነዚህ በረከቶች ተካፋይ ሆነው የተነገረላቸው እነጳውሎስና አጠቃላይ የቆሮንቶስ ቅዱሳን ሁሉ ሲሆኑ፤ ይህም ማለት አገልጋዮችም ሆኑ የሚገለገሉት ሰዎች ሁሉ የዚህ በረከት ተካፋዮች ናቸው ማለት ነው፡፡
8. በአገልጋዮችና በተገልጋዮች መሃል የነበረው ግንኙነት፤ ጳውሎስና ሃዋርያ ሆኖ ሳለና ምን ማድረግ እንደሚገባቸው እንኳን ማዘዝ ሲችል የቆሮንቶስ ሰዎች በራሳቸው እምነት እነደሚቆሙ በመቀበል ለደስታቸው ከእነርሱ ጋራ እንደሚሰራ እንጂ፤ እርሱም ሆነ ከእርሱ ጋራ ያሉት በእነርሱ ላይ የሚሰለጥኑ እንዳልነበሩ እናያለን፡፡

## ጥናት ሶስት 2ኛ ቆሮ 2፡1-17 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በአራቱ ቁጥሮች ላይ ትኩረት ተሰጥቷቸው የሚታዩት ቃላት ሃዘንና ደስታ የሚሉት ናቸው፡፡ ለጳውሎስ ወደ ቆሮንቶስ ላለመሄድ ምክንያት ሆኖ በቁ1 ላይ የተጠቀሰው ነገር ‹‹ላሳዝናችሁ ስላልፈለግሁ›› የሚለው ሃሳብ ነው፡፡
2. ከነዚህ ቁጥሮች እንደምረዳውና እንደሚመስለኝ ከሆነ፤ የነበረውን ሁኔታ በጽሁፍ ከፈታ ወይም ካረገበ በኋላ ፊት ለፊት በሚያገናቸው ሰዓት እርስ በእርሳቸው አንዳቸው የሌላቸው ደስታ ምንጭ የሚሆኑበት እንጂ የሃዘን ጊዜ እንዲሆን ስላልፈለገ ይመስላል ቁ3፡፡ በአገልግሎቱ የሚጠቀሙ ሰዎችና የሚያገለግሉ ሰዎችም ጭምር ከወንጌል የሚገኘውን ደስታ ተካፋዮች ሊሆኑ እንደሚገባ እንመለከታለን፡፡
3. ደብዳቤውን ሲጽፍ፤ በትልቅ ሃዘን፣ በልብ ጭንቀት፣ በብዙ እንባ ነው ያደረገው፡፡ ጽሁፉ እነርሱን እንደሚያሳዝን ያውቃል እላለሁ፤ ምክንያቱም እርሱ ለመጻፍ ያለፈባቸው በቁ4 ላይ የምናነባቸው ስሜቶቹና እንደገና ደግሞ ከቁ1-4 ያሉትን አጠቃላይ ሃሳቦች ስንመለከት እርሱ ያደረገው ነገር ሊያሳዝናቸው እንደሚችል የተረዳ መሆኑን ደንበኛ ፍንጭ ይሰጠናል፡፡
4. እንዲረዱለት የፈለገው ዋነኛ ነገር ደብዳበው ከፍቅር የመነጨ እንጂ እነሱን ለማሳዘን የታሰበ እንዳልሆነ ነው፡፡ ከምሳ 27፡6 እንደምንረዳው እወድሃለሁ እያለ ስንጠፋ ከማይመልሰን ይልቅ እውነቱን ነግሮን ቢያሳዝነን እንደሚመረጥ፣ ኤፌ. 4፡15ትም ይህንኑ ሃሳብ በሌላ መልኩ እንደሚያቀርብልን ሁሉ፤ ጳውሎስም ፍቅሩን አይቶ እንዳላየ በማለፍ ሳይሆን፣ እውነትን በፍቅር በመንገር ነው የገለጠላቸው፡፡
5. ቅዱሳኑ እንዲያደርጉ የሚጠየቋቸው ነገሮች፡ ይቅር እንዲሉት፣ እንዲያጽናኑትና፣ ፍቅራቸውን እንዲገልጡለት ነው፡፡ ቅጣቱን የወሰኑት ከቆሮንቶስ ቅዱሳን አብዛኛዎቹ እንደሆኑ ይታያል፡፡ ከነዚህ ቁጥሮች የተማርኩት፤ ከማህበር ሰዎችን የማስወገድና የመቅጣት ነገር በቅዱሳን ሁሉ የሚደረግ እንደሆነ ስማር፤ ሌላ ደግሞ ሃጥጣተኛ አዎን በድያለሁ ብሎ እውነተኛ ንስሃ ሲገባ ይቅር ማለት፣ ማጽናናትና ፍቅርን መግለጽ ከቅዱሳን እንደሚጠበቅ ተምሬአለሁ፡፡
6. ይቅርታንና ሰይጣንን ጳውሎስ ያገናኘው፤ አማኞች ይቅርታን ለመስጠት ሲቸገሩና እንቢ ሲሉ ለሰይጣን መግቢያ ቀዳዳን እየሰጡት እንደሆነ ነው የሚያስተምረው፡፡ ይቅርታን ለማድረግ እንቢ በማለቱ ይህ አማኝ የሳተው አንድ ትልቅ ነገር ቢኖር ይቅርታ አለማድረግ የሰይጣን ዕቅድ እንጂ የእግዚአብሄር ሃሳብ አለመሆኑን ነው፡፡
7. ቲቶን በዚያ ስላላገኘ መንፈሱ ሊያርፍ አልቻለም፤ ስለዚህም ተነስቶ ወደ ቲቶን ፍለጋ ወደ መቄዶንያ መሄድ ነበረበት፡፡ ጳውሎስ የተጽናናው በ2ኛ ቆሮ 7፡6-7 መሰረት በቲቶ መምጣትና የቆሮንቶስ ቅዱሳን ቲቶን ስላጽናኑት ነው፡፡ ጳውሎስ አዲሶች ወንጌልን እንዲሰሙ ታላቅ ቅናት እንዳለው ሁሉ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ቅዱሳን ታንጸውና በክርስቶስ በመቀደስ ሲያድጉ ማየትም ያንኑ ያህል ትጋት እንደሚያደርግ እንመለከታለን፡፡
8. ለሚጠፉትና ለሚድኑት የተለያየ አይነት ሽታ የሚሸት፣ ወንጌልን ለትርፍ ሲል የማይሸቃቅጥ፣ ከእግዚአብሄር እንደተላከ ሰው ወንጌልን የሚናገር፣ ወንጌልን በቅንነት የሚናገር…፡፡
9. ለሰይጣን መግቢያ መንገድ የሚሰጠው ዋነኛ ነገር ይቅር አለማለት ነው፡፡

# ጥናት አራት 2ኛ ቆሮ 3፡1-18 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. የቆሮንቶስ አማኞች ከነጳውሎስ ወንጌልን ሰምተው ያመኑና ክርስቶስ በህይወታቸው እየሰራ እንዳለ በግለጽ የሚታይ ስለሆነ ለወንጌል አገልጋይነታቸው የተለየ ማስረጃ እንደማያስፈልግ ነው፡፡ አማኝ ሁሉ ሰዎች አካሄዳችንንና አረማመዳችንን ሁሉ የሚመለከቱት፣ ልክ እንደጽሁፍ ደግሞ ህይወታችንን የሚያነቡት እንደሆነ እያወቅን በጥንቃቄ ልንራመድ ይገባናል፡፡
2. ለዚህ አይነቱ አገልግሎት ብቁነት የሚገኘው ከእግዚአብሄር እንጂ ሰው በራሱ ብቁ ሊሆን እንደማይችል ይህ ቁጥር ያረጋግጥልናል፡፡ እነዚህ ሁለት የተለያዩ ጥቅሶች ይሁኑ እንጂ የሚያስተላልፉት ሃሳብ አንድ ነው፤ ይህም መንፈሳዊ ስራን እሰራለሁ የሚል ሰው ምን ጊዜም በእግዚአብሄር መንፈስ ሃይል እንጂ በራሱ ማድረግ የሚችለው ነገር ሊኖር እንደማይችል መረዳት እንደሚኖርበት ያስተምሩናል፡፡
3. የብሉይ ኪዳን አገልግሎት በፊደል ላይ የተመሰረተ ሲሆን፤ የአዲስ ኪዳን አገልግሎት ደግሞ በመንፈስ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ እኔ እንደሚገባኝ ከሆነ ‹‹ፊደል›› ሲል የብሉይ ኪዳንን ህግጋት ለማለት ሲሆን፤ ‹‹መንፈስ›› ሲል ደግሞ የአዲስ ኪዳንን የወንጌል መልዕክት ለማመልከት ይመስለኛል፡፡
4. የብሉይ ኪዳን አገልግሎት የተጠቀሰባቸው፡ ከጊዜ በኋላ የሚያልፍ፣ በድንጋይ ላይ በፊደል የተቀረጸ፣ የሞት አገልግሎት፣ የሚኮንን አገልግሎት፣ ክብር የሌለው፣ የሚያልፍ በሚሉት ተጠቅሷል፡፡ የአዲስ ኪዳኑ አገልግሎት ደግሞ፡ የመንፈስ አገልግሎት፣ የሚያጸድቅ አገልግሎት፣ የላቀ ክብር ያለው፣ ጸንቶ የሚኖር አገልግሎት በመባል ተነግሯል፡፡
5. ጳውሎስ በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ስለብሉይ ኪዳን የበታችነት ሲናገር አላስፈላጊነቱን ወይም ደግሞ ምንም ጥቅም የለውም ለማለት አይደለም፤ ነገር ግን የአዲስ ኪዳኑ አገልግሎት ምን ያህል ክቡርና እጅግ የላቀ መሆኑን ለማሳየት የማነጻጸር ዘዴን የመጠቀም ጉዳይ ነው፡፡
6. የአዲስ ኪዳን አገልጋዮች በድፍረት መናገር የሚያስችላቸው ምክንያት ያላቸው የተስፋ ዓይነት ነው፡፡ ጳውሎስ በዚህ ክፍል በተለይም በቁ12 ላይ ተስፋ እያለ የሚናገረው ነገር ከላይ በማነጻጸር ያስቀመጣቸውን ግሩም ሃሳቦች ነው ብዬ አምናለሁ፡፡
7. መጋረጃው ሊወገድ የሚችልበት ከሰው አንጻር አንድ መንገድ ብቻ እንዳለና ይህም መንገድ ወደ ጌታ ዘወር ማለት ሲሆን (ቁ14 እና 15)፤ በ2ኛ ቆሮ 4፡6 ላይ ደግሞ ከእግዚአብሄር አንጻር ደግሞ እርሱ ራሱ በሰዎች ህይወት ብርሃኑን ይብራ ብሎ መጋረጃውን ካላስወገደ ሰው የወንጌልን እውነት ማየት እንደማይችል መረዳት እንችላለን፡፡
8. 1) ሙሴ በቁ13 ላይ እንደምናነበው አገልግሎቱ በተሸፈነ ፊት እንደነበረ ሲሆን፤ የእኛ አገልግሎት ግን ይህ ቁጥር እንደሚነግረን ባልተሸፈነ ፊት ነው፡፡ 2) እያገለገልን የእኛም ህይወት ደግሞ እርሱን እንዲመስል ከክብር ወደ ክብር እንለወጣለን፡፡ 3) ጌታ ራሱን እንመስል ዘንድ በእኛ ህይወት ውስጥ ይሰራል፡፡

# ጥናት አምስት 2ኛ ቆሮ 4:1-18 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በዚህ ሥፍራ ‹‹ይህ አገልግሎት›› በማለት የሚናገረው በምዕ 3 ላይ የዘረዘረውን የከበረና የሰዎችን ህይወት መቀየር ሃይል ያለውን አገልግሎት ነው፡፡ ይህንን አገልግሎት የተቀበለ ሰው አሳፋሪ ነገሮችን መተው ይጠበቅበታል፣ ማታለልና የእግዚአብሄርን ቃል ከሃሰት ጋራ መቀላቀል አይችልም፣ እውነትን በግልጽ ይናገራል፣ በሰው ሁሉ ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖረው ራሱን በእግዚአብሄር ፊት ያቀርባል፡፡
2. ይህንን ማለቱ ለእኔ እንደሚገባኝ፤ በሰዎች ዘንድ ተቀባይነት ለማግኘት መልዕክታችንን መበረዝ፣ ከሃሰት ጋራ መቀላቀል ወይም ደግሞ ማናቸውንም ዓይነት በሰው ጥበብ ሊደረጉ የሚችሉትን ነገሮች በማድረግ ሰዎችን ለማሳመን ጥረት ከማድረግ ይልቅ፤ እውነተኛውን የወንጌል መልዕክት ሰዎች ቢወዱት ቢጠሉት፣ ቢቀበሉት ባይቀበሉት፣ ቢያከብሩት ቢንቁት እውነቱን ልክ እግዚአብሄር እዚያው ቆሞ እንደሚያይና እንደሚሰማን አድርገን ወንጌሉን እንናገራለን ለማለት የፈለገ ይመስለኛል፡፡
3. በቁ3 ላይ የሚጠፉ ሲላቸው፤ በቁ4 ላይ ደግሞ የማያምኑ ይላቸዋል፡፡ እነዚህ ሁለቱ አይነት ሰዎች የተለያዩ ግሩፖች ሳይሆኑ አንድ አይነት ሰዎች ናቸው፤ የማያምኑት ሰዎች ራሳቸው ናቸው የሚጠፉ ሰዎች ተብለው በሌላው ቁጥር ላይ የሰፈሩት፡፡
4. በቁ4 ላይ ሰይጣን ስራው ሰዎች ወንጌልን አምነው እንዳይድኑ አይናቸውን ማሳወር ሲሆን፤ በቁ6 ላይ ደግሞ በአንጻሩ እግዚአብሄር የሰው ልጆች የወንጌልን እውነት አምነው ህይወትን እንዲያገኙ የሰዎችን አይን በመክፈት ብርሃንን በልባቸው ያበራል፡፡ የወንጌል አገልጋይ ተሳትፎው ወንጌልን በቁ1-3 ጳውሎስ በሚናገረው አይነት መናገርና ውጤቱን ለእግዚአብሄር መተው ነው ብዬ አምናለሁ፡፡
5. ለወንጌል የተሰጡት ሁለት ስሞች ‹‹እጅግ ታላቅ ሃይል›› እና ‹‹የከበረ ነገር›› የሚሉት ናቸው፡፡ እንደዚህ የከበረውንና እጅግ ታላቅ የሆነውን ነገር እግዚአብሄር ሊያስቀምጥ የወደደው በሸክላ እቃ ውስጥ ነው፡፡ ይህ የእግዚአብሄር ድርጊት ጳውሎስ በቁ1 ላይ ለምን እንደዚህ አይነት አገልግሎት እንደተቀበልን ሲያስረዳ የተጠቀመበት ቃል ሁኔታውን ግልጽ ያደርግልናል፤ ይህም ‹‹ከእግዚአብሄር ምህረት የተነሳ›› የሚለው ሃሳብ ነው፡፡
6. በመጀመሪያ ደረጃ ተጠቃሚዎች ሆነው የምናያቸው የወንጌል አገልጋዮች ራሳቸው ናቸው (ቁ14)፤ ጥቅማቸውም ከሙታን ተነስተው በኢየሱስ ፊት ለሽልማት መቆማቸው ነው፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ወንጌል የተሰበከላቸው ሰዎች ተጠቃሚዎች ሲሆኑ (ቁ12፣ 15)፡፡ ሌላው ተጠቃሚ እግዚአብሄር ራሱ እንደሆነ በቁ15 ላይ እንመለከታለን፤ እርሱም ለስሙ ክብር በምስጋና ላይ ምስጋና ይጨመርለታል ማለት ነው፡፡
7. የአሁኑን መከራችንን ቀላልና ጊዜያዊ ይለዋል፤ የሚያስገኝልን ነገር ደግሞ ወደር የማይገኝለትና፣ ዘለዓለማዊ በማለት ይናገራል፡፡ በዓውደ ምንባቡ መሰረት የሚታይና ሲል መከራውን ሲሆን፤ የማይታይ ደግሞ፤ መከራው የሚያስገኝልን ነገሮች ነው፤ ሆኖም ሰፋ ተደርጎ ሲታይ ማናቸውንም የሚታይ ነገር ሊጠቀልል እንደሚችልና የማይታየውም እንዲሁ የማይታየውን ይጠቀልላል፡፡
8. የሚያነጻጽራቸው ሁለት ነገሮች  ውጫዊና ውስጣዊ ሰውነታችንን ነው፡፡ እንደ እኔ አመለካከት ከሆነ በውጫዊው ሰውነታችን የሚካሄደው እርጅና ወይም እየጠፉ መሄድን ለማቆም ምንም ዓይነት ቋሚ የሆነ ልንቆጣጠር የምንችልበት መንገድ እንደሌለ፤ ነገር ግን በውስጥ ሰውነታችን የሚካሄደውን እለት በእለት የመታደስ ሁኔታ ልንገታውም ሆነ ልናፋጥነው በራሳችን እጅ እንዳለ አምናለሁ፡፡

# ጥናት ስድስት 2ኛ ቆሮ 5፡1-10 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በዚህ ክፍል ውስጥ እያነጻጸረ የሚናገረው ስለምድራዊ ድንኳናችንና ስለሰማያዊው ቤታችን ነው፡፡ ስለ ምድራዊው ድንኳናችን የሚናገረው አንድ ነገር ቢኖር ፈራሽ ወይም ጊዜያዊ እንደሆነ ሲሆን፤ ስለ ሌላኛው መኖሪያችን ደግሞ በሰው እጅ እንዳልተሰራ፣ ከእግዚአብሄር እንደሆነ፣ ዘለዓለማዊ ቤት እንደሆነና ይህም ቤት በሰማይ እንዳለ ያረጋግጥልናል፡፡
2. ሰማያዊ መኖሪያችንን የምንለብሰው የምድራዊው ድንኳናችን ሲፈርስ ወይም ስንሞት ነው፡፡ ‹‹ሰማያዊ መኖሪያ›› ሲል በ1ኛ ቆሮ 15፡54 ላይ እንደሚናገረው አዲስና የማይሞተውን ሰውነታችንን የመልበሳችን ነገር ነው፡፡ ይህ እስከሚሆንበት ጊዜ ድረስ የምናደርገው ነገር ቁ2 እንደሚነግረን የሰማዩን መኖሪያችንን ለመልበስ እየናፈቅን እንቃትታለን፡፡
3. ‹‹ምድራዊ ድንኳን›› ሲል ስለሰውነት እንደሚናገር የሚጠቁመን በቁ4 ላይ ያለው ‹‹ሟች የሆነው›› የሚለው ሃሳብ ሲሆን፤ በተጨማሪም ደግሞ ስለልብስ መናገሩም ተጨማሪ መረጃ ይሆነናል፡፡ ቁ3-4 እንደሚገባኝ ከሆነ ሰውነታችን በማናቸውም ጊዜ ያለልብስ ራቁቱን ሆኖ የሚገኝበት ጊዜ እንደማይኖርና፤ ሌላው ደግሞ ከዚህ ሰውነታችን መገላገል ብንፈልግም እንኳን ከዚያ በላይ ግን የምንናፍቀው ነገር ለማያዊውን መኖሪያችንን መልበሳችን እንደሆነ ነው የምረዳው፡፡
4. ‹‹ለዚህ ዓላማ›› በመባል የተነገረው ከላይ ባሉት ቁጥሮች ላይ እንደተነገረው የሚፈርስና የሚበሰብስ ምድራዊ መኖሪያ ድንኳን እንዲኖረን ብቻ ሳይሆን፤ በእጅ ያልተሰራና ዘለዓለማዊ ልብስ እንዲኖረን አድርጎ ሲሰራን የእግዚአብሄር ዓላማ እንደነበረ ሲያሳየን ነው፡፡
5. ሐዋርያው ህይወቱን የሚኖረው በእምነት እንደሆነ ቁ6 ና ቁ7 ያሳዩናል፤ ለዚህም ምክንያት ሆኖ የማየው ነገር በተለይም ቁ5 ላይ በመያዣነት የተሰጠው መንፈስ ቅዱስ ስላለው እርግጠኛ የሚሆንበት ነገር አለው፡፡
6. አንደኛው ከጌታ ተለይቶ ማለትም በስጋ በምድር መኖር ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ ከስጋ ተለይቶ ከጌታ ጋራ መሆን ናቸው፡፡ የጳውሎስ ምርጫ ከጌታ ጋራ መሆን እንደነበረ ስንመለከት፤ በቁ8 ላይ ስናነብ ደግሞ ጳውሎስ ይህ የእርሱ ምርጫ የሁሉም አማኝ ምርጫ እንደሚሆን በእርግጠኝነት ይናገራል፡፡
7. ጳውሎስ በእነዚህ በሁለት ነገሮች መሃል ልዩነት እንደሌለ አድርጎ የሚያየው በሁለቱም ሁኔታዎች ውስጥ የጋራ የሆነው ነገር በሞቱም ሆነ በህይወቱ የእርሱ ዓላማ እግዚአብሄርን ማስደሰት መሆኑ ነው፡፡ ‹‹ዓላማችን›› እና ‹‹ሁላችን›› እያለ ሲናገር አማኞች ሁሉ በመወከል ነው፤ ምክንያቱም ጠቅላላ ምዕራፉን ስናነብ በአማኞች ላይ ያተኮረና ያላመኑ ሰዎችን ያስገባበት ሁኔታ ስለማናይ ነው፡፡
8. በኤፌሶን ላይ የመናገረው ደህንነት በጸጋ እንጂ በስራ እንዳልሆነና ከእግዚአብሄር በምድር እያለን የተቀበልነው ሲሆን፤ ይህ ክፍል የሚናገረው ግን ከዳንን በኋላ የምናደርገው ተግባር በእግዚአብሄር ፊት አስፈላጊ እንደሆነና በእርሱ ዘንድ ዋጋም እንዳለው የሚጠቁመን ነው፡፡ ቁ9ን የሚለማመድ ማለትም ህይወቱን እግዚአብሄርን በማስደሰት ዓላማ የሚመራ ሰው ይህ ቁጥር ያስፈራዋል ብዬ አላምንም፡፡

# ጥናት ሰባት 2ኛ ቆሮ 5፡11-21 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በዚህ ቁጥር ላይ ‹‹ጌታን መፍራት›› እያለ የሚናገረው በቁ10 ጋራ ያለውን ሰዎች ሁሉ ለፍርድ በክርስቶስ ፍርድ ወንበር ፊት መቅረባቸውን አስመልክቶ ነው፡፡ በቁ11 ላይ ከጳውሎስ አነጋገር እንደምናየው አማኞች ሁሉ ይህንን ቀን በግድየለሽነት እንዳይመለከቱት የተቻለውን ሁሉ በማድረግ ላይ እንደሚገኝ እንረዳለን፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ጌታን መፍራት የሚባለው ነገር ስለገባው ሌሎችም የዚህ ፍርሃት እንዲያድርባቸው ለማድረግ ይጥራል፡፡ ዕብ ዕብ 12፡29
2. ስለነጳውሎስ ማንነት በእግዚአብሄር ዘንድ የተደበቀ ነገር ስለሌለ ግልጽ ሲሆን፤ በቆሮንቶስ ሰዎችም ዘንድ ደግሞ እንዲሁ ግልጽ መሆኑን እርግጠኛ ባይሆንም እንኳን ተስፋ የሚያደርገው ያንን ነው፡፡ በልብ ንጽህና የሚሰሩ እንደሆኑ መናገር ያስፈለገበት ምክንያት የቆሮንቶስ ምዕመናን ትክክለኛና ለእነርሱ የሚያስቡ ቅን አገልጋዮች እንዳላቸው እንዲረዱ፣ እንዲሁም ትምክህታቸውን በውጫዊ ነገር አድርገው እናገለግላችኋለን ለሚሉት መልስ እንዲኖራቸው እንጂ ለፉከራ ያደረጉት ነገር እንዳልሆነ እንዲያውቁ ነው የፈለገው፡፡
3. እነዚህን ሁለት ሰዎች የሚያመሳስላቸው ነገር፤ ሁለቱም በአገልግሎታቸው አዕምሮውን እንደሳተ ሰው ሆነው መቆጠራቸው ነው፡፡ እግዚአብሄርን በመታዘዝ መንፈሳዊ ቅናት በተሞላው መልኩ የሚያደርጓቸው ነገሮች በሰዎች ዘንድ እንደ እብድ ሊያቆጥራቸው እንደሚችል፤ እንደ እብድም ተቆጥረው ለእግዚአብሄር  የሚያደርጓቸው ነገሮች ለሌሎች የደህንነት ወይም የመንፈሳዊ ህይወት እድገት ውጤት ያስገኛሉ፡፡
4. ሁሉም ከሞተላቸው ኢየሱስ ጋራ ይሙቱ እንጂ፤ የሞተላቸው ከሙታን ሲነሳ ሁሉም ከእርሱ ጋራ የተነሱ ስለሆነ (ሮሜ6፡5)፤ በዚህ ክፍል ‹‹በህይወት ያሉት›› እያለ የሚናገረው ከእርሱ ጋራ ከሙታን ስለተነሱት ነው፡፡ በእርሱ ባመኑት ሰዎች ውስጥ መከሰት የሚኖርበት ነገር ቁ15 እንደሚጠቁመን ከእርሱ ጋራ የሞቱት ሰዎች ሁሉ ከእንግዲህ ወዲያ የሚኖሩት ለራሳቸው ሳይሆን ለሞተላቸው ለየሱስ እንደሆነ ያረጋግጥልናል፡፡
5. ‹‹ስለዚህ ከአሁን ጀምሮ›› የሚለው አነጋገር የሚጠቁመን ክርስቶስ እንደሞተልን ተረድተን ለራሳችን ከመኖር ይልቅ ለእርሱ መኖር የወሰንበትን ጊዜ ያመለክታል፡፡ እነዚህ ሰዎች ለክርስቶስ እንጂ ለራሳቸው ያለመኖራቸውን የሚያረጋግጡበት አንደኛው መንገድ ማንኛውንም ሰው በውጫዊው ሁኔታው መመዘን ማቆማቸውና ክርስቶስ እርሱን በሚያይበት ዓይን የማየት ችሎታን ያዳብራሉ፤ ይህም ማለት ሚዛናቸውና አመለካከታቸው ተቀይሯል ማለት ነው፡፡
6. እነዚህን ሁለት ክፍሎች በአንድነት ስናነብ በክርስቶስ መሆን ማለት ልክ ቅርንጫፍ በወይኑ ግንድ ላይ ተጣብቆ መሞቱና መኖሩ ከዚያ ግንድ ጋራ የማይነጣጠል እንደሆነ፤ በክርስቶስ መሆን ማለትም ይህንኑ ይመስላል፡፡ ከእግዚአብሄር እንደሆኑ የሚናገራቸው ነገሮች አዲስ ፍጥረት መሆናችን፣ አሮጌውን ያሳለፈና ሁሉን አዲስ ያደረገው እርሱ ነው፣ ከራሱ ጋራ ያስታረቀን፣ የማስታረቅን አገልግሎት የሰጠን እሱ ነው፡፡
7. ‹‹እርቅ›› የሚለው ቃል ነው፡፡ ከእግዚአብሄር ጋራ እርቅ ያደረጉ ሰዎችን አስመልክቶ የተነገሩት ነገሮች፤ የማስታረቅ አገልግሎት ተሰጥቷቸዋል፣ የማስታረቅ ቃል ተሰጥቷቸዋል፣ የክርስቶስ እንደራሴዎች ሆነዋል፣ በእነርሱ አማካኝነት እግዚአብሄር ጥሪውን ያቀርባል፣ ከእግዚአብሄር ጋራ ታረቁ ብለው ይለምናሉ፡፡
8. ከአገሪቱ መሪ የተቀበለውን መመሪያ ሥራ ላይ ያውላል፣ የአገሪቱን መሪ በተላከበት ሃገር ላይ ይወክላል፣ አምባሳደር በሌላ ሃገር ውስጥ ይኑር እንጂ የሚተዳደረው በዚያ ሃገር ህግ አይደለም፣ የአምባሳደር በአንድ ሃገር ውስጥ መኖርና አለመኖር የሃገሮቹን የጓደኛነት ጥልቀት ያሳያል፡፡

# ጥናት ስምንት 2ኛ ቆሮ 6፡1-18 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ጳውሎስ በዚህ ክፍል አማኞችን የሚያስተዋውቃቸው ከእግዚአብሄር ጋራ አብረው የሚሰሩ ሰዎች እንደሆኑ ነው፡፡ አብረው የሚሰሩትም ነገር በ5፡20 ላይ የሚናገረውን የእርቅ ነገር ሲሆን፤ እግዚአብሄር ዓለምን ከራሱ ጋራ ለማስታረቅ በሚያደርገው ሥራ ውስጥ እኛም ከእግዚአብሄር ጋራ ታረቁ በማለት የእርሱ አምባሳደር በመሆን ለሰዎች ሁሉ ጥሪውን እናስተጋባለን ማለት ነው፡፡
2. ይህ የእግዚአብሄር ጸጋ በመባል በዚህ ክፍል የተነገረው በወንጌል በማመን እኛ የተቀበልነውን የደህንነት ህይወት ሲሆን፤ በኢሳ 49፡8 ካለው ሃሳብ ጋራ የሚገናኘውም እኛ በትክክለኛ በእግዚአብሄር ሰዓት እርሱ እንደተቀበለንና እንዳዳነን ሁሉ፤ ለሌሎችም እግዚአብሄር በእኛ በኩል ጥሪውን ሊያቀርብላቸው ለሚፈልጋቸው ሰዎች ትክክለኛ የመዳን ሰዓታቸው ወደፊት ቀጠሮ የሚሰጠው ሳይሆን አሁን በመሆኑ አስቸኳይነቱን ሲያስረዳን ነው፡፡
3. በዚህ ቁጥር ላይ እንዲያውቁለት የፈለገው ነገር አገልግሎቱ እንዲነቀፍበት እንደማይፈልግና፤ ስለዚህም ለማንም እንቅፋት መሆን እንደማይፈልግ ነው፡፡ በነዚህ ሁለት ክፍሎች የማየው በዚህ ክፍል በራሱ ላይ አተኩሮ የሚናገር ሲሆን፣ በ1ኛ ቆሮ ግን ሌሎችን ሲመክር ይታያል፤ በዚህ ክፍል ለአገልግሎቱ ሲባል ሲሆን በሌላው ግን ለደካማ ወንድም ሲባል ነው፤ ሌሎችንም ሃሳቦች መጨመር ይቻላል፡፡
4. በትዕግስት፣ በመከራ፣ በችግር፣ በጭንቀት፣ በመገረፍ፣ በመታሰር፣ በሁከት፣ በስራ ብዛት፣ እንቅልፍ ማጣት እና መራብ… እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡
5. በምድራዊ አመለካከት ብዙ ንብረትና ቁሳቁስ እንደሌላቸው፤ ነገር ግን በራዕ 3፡17 ሲናገር እግዚአብሄር ባለጠግነት በሚለው መለኪያ ሲመዘኑ ባለጠጎች እንደሆኑና ሌሎችንም ደግሞ ባለጠጎች የሚያደርጉ እንደሆኑ ሲናገር ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ ከዚሁ ጋራ ተመሳሳይ ሲሆን ሁሉ የእርሱ የሆነው ክርስቶስ በውስጡ ያለው ሰው ደግሞ ለሰዎች ምንም የሌለው ቢመስልም ሁሉ የሞላው ሰው መሆኑን ሲያረጋግጥ ነው፡፡
6. ሁሉን ነገር ግልጽ በሆነ መንገድ ነግረዋቸዋል፣ ልባቸውን ወለል አድርገው ከፍተውላቸዋል፣ ፍቅራቸውንም አልነፈጓቸውም፡፡ ከቆሮንቶስ አማኞች የሚለምኑት አንድ ነገር ቢኖር እነርሱም ልባቸውን ወለል አድርገው እንዲከፍቱላቸውና ፍቅራቸውን እንዳይነፍጓቸው ነው፡፡ ከዚህ ክፍል የማየው አገልጋዮቹ ምን ያህል ለምዕመናኑ ፍቅር እንዳላቸውና፤ በሌላ በኩል ደግሞ የምዕመናኑን ፍቅር ምን ያህል እንደሚጠሙ እመለከታለሁ፡፡ የዘመናችን ችግር ባብዛኛው የተገላቢጦሽ ይመስለኛል፡፡
7. በዚህ ክፍል የሚያስጠነቅቃቸው ከማያምኑ ሰዎች ጋራ አግባብ ባልሆነ መንገድ እንዳይጠመዱ ነው፡፡ ከማያምን ሰው ጋራ አግባብ በሌለው መንገድ መጠመድ፤ ትዳር ሊሆን ይችላል፣ የንግድ ነገር ሊሆን ይችላል፡፡ በማነጻጸሪያነት የተጠቀመባቸው፡ ጽድቅና ዐመጽ፣ ብርሃንና ጨለማ፣ ክርስቶስና ቤልሆር፣ የሚያምንና የማያምን፣ ቤተመቅደስና ጣዖት ናቸው፡፡
8. በ1ኛ ቆሮ 6፡19 ላይ ያለው ጥቅስ ቤተመቅደስ በማለት እያንዳንዱን አማኝ በተናጠል የእግዚአብሄር ማደሪያ አድርጎ የሚናገር ሲሆን፤ በ2ኛ ቆሮ 6፡16 ላይ ግን አማኞችን ሁሉ እንደ አንድ ወስዶ በብዙ ቁጥር በማጠቃለል የክርስቶስ አካል የእግዚአብሄር ማደሪያ እንደሆነ የሚናገር ነው፡፡
9. ቤተመቅደስ የመሆን ጥቅሞቹ፤ የእግዚአብሄር ከእኛ ጋራ መኖር፣ በመካከላችን መመላለስ፣ አምላካችን መሆኑ፣ ተቀባይነት ማግኘታችን፣ አባታችን መሆኑ፣ ወንድና ሴት ልጆቹ መሆናችን ሲሆኑ፤ ሃላፊነቶቹ ደግሞ ከማያምኑ ሰዎች ጋራ በማይሆን መንገድ አለመጠመድ፣ ከአህዛብ መሃል መውጣት፣ ለእግዚአብሄር መለየት፣ ርኩስን አለመንካትና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

# ጥናት ዘጠኝ 2ኛ ቆሮ 7፡1-16 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በማበረታቻነት የተነገረው ነገር ለእግዚአብሄር ህዝብ ጌታ ራሱ የገባው የተስፋ ቃል ነው፡፡ የተስፋ ቃል በማለት ጳውሎስ የሚናገረው በ2ኛ ቆሮ 6፡16-18 ላይ ከእነርሱ ጋራ እኖራለሁ፣ በመካከላቸው እመላለሳለሁ፣ አምላካቸው እሆናለሁ፣ እቀበላቸዋለሁ፣ አባት እሆናቸዋለሁና የመሳሰሉት ናቸው፡፡ ሌላው ለቅድስና ማበረታቻ ሆኖ የተነገረው ሃሳብ የእግዚአብሄር ፍርሃት ወይም አክብሮት የሚለው ሃሳብ ነው፡፡
2. ጳውሎስ ከቆሮንቶስ ሰዎች እየለመነ ያለውና እስከዚያን ጊዜ ድረስ እንዳላገኘ ሆኖ የሚሰማው ነገር የልባቸውን በስፋት መከፈት ነው፡፡ እኔ እንደሚመስለኝ ምናልባት የቆሮንቶስ ሰዎች ልባቸውን በስፋት አልከፍት ያሏቸው የነጳውሎስ ከሳሾች በነዚህ በተዘረዘሩት ነገሮች የሚከሷቸው ሳይሆን እንደማይቀርና ወይም ደግሞ እነዚያ ከሳሾቻቸው በነዚህ አማኞች ላይ እያደረጉ ያሉትን ነገሮች በተዘዋዋሪ የማጋለጥ አነጋገር ሊሆን እንደሚችል አስባለሁ፡፡
3. ይህንን እውነት ለማረጋገጥ ጳውሎስ የተጠቀመበት አነጋገር ቢኖሩም ቢሆን ቢሞቱም አብረው እንደሆነ፤ ማለትም የቆሮንቶስ ሰዎች ሞት ማለት የነጳውሎስ፣ የቆሮንቶስ ሰዎች ህይወት ማለት ለነጳውሎስ ህይወት እንደሆነ ነው፡፡ ይህ አነጋገሩ የሚያስታውሰኝ ያዕ 1፡2 ‹‹ወንድሞች ሆይ ልዩ ልዩ መከራ ሲደርስባችሁ እንደ ሙሉ ደስታ ቁጠሩት›› የሚለውን ጥቅስ ነው፡፡
4. በዚህ ክፍል የተጠቀሰው የእግዚአብሄር ባህርይ ‹‹የማጽናናት አምላክ›› እንደሆነ ነው፡፡ እነጳውሎስን ያጽናናበት መንገዶች ሁለት ሲሆኑ አንደኛው በቲቶ መምጣት ሲሆን፣ ሌላው ደግሞ ቲቶ በቆሮንቶስ አማኞች ስለተጽናና የእርሱ መጽናናት ለነጳውሎስ መጽናናት ሆኗል፡፡
5. ጳውሎስ የተደሰተው የቆሮንቶስ ሰዎች ስለሚናፍቁት፣ የቆሮንቶስ ሰዎች ስላዘኑና እነዚህ አማኞች ለእርሱ ስላላቸው ቅናት ከቲቶ ሰምቶ ነው፡፡ ይህ አይነቱ ሃዘን ‹‹እንደ እግዚአብሄር ፈቃድ የሆነ ሀዘን›› በመባል በቁ9፣ 10፣ 11 ላይ ተጠቅሷል፡፡
6. እንደ እግዚአብሄር ፈቃድ የሆነ ሃዘን ማለት ንስሃ ለመግባት የሚያበቃ ሃዘን ቁ9፤ ሰዎችን የማይጎዳ ቁ9 ፤ ቁ10 እና በተጨማሪም የዚህ ዓይነቱ ሃዘን ወደ ደህንነት የሚያደርስ ደግሞም ጸጸት የሌለበት ዓይነት ሃዘን ነው፡፡ እንደ እግዚአብሄር ፈቃድ የሆነ ሃዘን የሚያስገኛቸው ነገሮች ደግሞ በቁ11 ላይ የሰፈሩት ትጋት፣ መልስ የመስጠት ችሎታ፣ ቁጣ፣ ፍርሃት፣ ናፍቆት፣ በጎ ቅናት፣ ተግሳጽ ናቸው፡፡ የዚህ ተቃራኒ ሃዘን ሰዎችን የሚሰብር ውስጥን የሚሰብርና የሚጎዳ፣ የማይጠግን አይነት ሃዘን ነው፡፡
7. በጳውሎስ ህይወት ደስታን ያመጡት ነገሮችን በአጠቃላይ ስንመለከት የቲቶ መምጣት፣ በቆሮንቶስ ሰዎች ለቲቶ የተሰጠው አቀባበል፣ የቲቶ ደስታ (13)፣ የቆሮንቶስ ሰዎች አስተማማኝነት (16)
8. ጳውሎስ ስለበዳይና ተበዳይ ለማስተካከል ከመሞከሩ በፊት ቅድሚያ የሰጠው ነገር በቆሮንቶስ አማኞችና በእነጳውሎስ ማለትም በአገልጋዮቹ መሃል የነበረውን ግንኙነት በማደስ ላይ ነበረ፡፡ የበዳዩንና የተበዳዩን ነገር ማቆየት ማለት ችግሩን መፍታት አያስፈልግም ማለት ሳይሆን ቅድሚያ ሊሰጠው የሚያስፈልገው ሌላ ነገር እንዳለና ለዚያ ቅድሚያ መስጠት እንደሚገባ ለማስረዳት ነው፡፡

# <u>ጥናት አስር 2ኛ ቆሮ 8፡1-24 (ለመሪው የተዘጋጀ)</u>

1. ስለመቄዶንያ አማኞች እንዲያውቁት የፈለገው ነገር እግዚአብሄር የሰጣቸውን ጸጋ ነው፡፡ በህይወታቸው ያመጣው ለውጥ በጽኑ መከራ ውስጥ ደስታ እንዲኖራቸው አርጓቸዋል፣ በብርቱ ድህነት ውስጥ የበዛ ልግስና እንዲያሳዩ አርጓቸዋል፣ ከአቅማቸው በላይ መስጠት እንዲችሉ አርጓቸዋል፣ ቅዱሳንን ለመርዳት ሳይለመኑ እንዲያውም እንዲለምኑ አርጓቸዋል፡፡
2. ሙሉ ለሙሉ ራሳችንን ሳንሰጠው ያለንን ነገሮች ማለትም እንደ ገንዘብ፣ ጊዜና የመሳሰሉትን ነገሮች ልንሰጥ እንደምንችል የታወቀ ነው፤ ከመቄዶንያ ክርስትያኖች እንደምንማረው ግን የመጀመሪያውና ቅድሚያ ልንሰጠው የሚገባን ነገር ቢኖር ራሳችንን ለእርሱ መስጠት እንደሚገባን ነው፤ ራሳችን ሳንሰጥ ያለንን ነገሮች መስጠት ብንሞክር ትርጉም የሌለው ነገር ይሆናል፡፡
3. ልቀው የተገኙባቸው ነገሮች በእምነት፣ በቃል፣ በእውቀት፣ በፍጹም ትጋት፣ ለነጳውሎስ ባላቸው ፍቅር ልቀው ተገኝተዋል፡፡ ከዚህ ጋራ አያይዞ በዚህ የቸርነት ሥራ ማለትም ቅዱሳንን በመርዳቱም ነገር ልቀው እንዲገኙ ያበረታታቸዋል፡፡
4. ሁለቱ ምሳሌዎች ሌሎችና ኢየሱስ ክርስቶስ ናቸው፡፡ ለምንወደው ሰው ያለንን ሁሉ ለመስጠት አይከብደንም ስለዚህም እጃችን የተፈታ ነው፡፡ ኢየሱስም ከፍቅሩ ጥልቀት የተነሳ ነው ለመስቀል ሞት እንኳን ራሱን አሳልፎ ለመስጠት እንቢ ያላለው፡፡
5. የጳውሎስ ፍርሃት የቆሮንቶስ ሰዎች ለተቸገሩ ወገኖች ለመስጠት ከአመት በፊት የገቡትን ቃል እንዳይረሱና ሳይፈጽሙ እንዳይቀሩ ነው፡፡ በዚህ ክፍል መሰረት ስጦታን ተቀባይነት እንዲያገኝ የሚያደርገው ነገር በበጎ ፈቃድ ከልብ የመስጠት ጉዳይ ሲሆን፤ አሰጣጣችንም ደግሞ ባለን መጠን እንጂ የሌለንን እንድንሰጥ እንደማይጠበቅብን እንማራለን፡፡
6. ይህ አነጋገር የሚጠቁመን አንዳችን ዛሬ ቢጎድልብንና ተቸግረን ሌላው ቢረዳን፤ ነገ ደግሞ በተራችን የሌላውን ጎዶሎ የምንሞላ እንደሆንን ይጠቁመናል፡፡ ይህ ክፍል አህዛብ በመንፈሳዊ ድህነት ውስጥ ሳሉ አይሁዶች መንፈሳዊ ነገርን እንዳከፈሏቸው፤ ዛሬ ደግሞ አይሁድ ለስጋ በሚያስፈልግ ነገር ድሆች ስለሆኑ አህዛብ ደግሞ ጎዶሏቸውን ሊሞሉ እንደሚያስፈልግ መማር እንችላለን፡፡
7. ገንዘቡን እንዲወስዱ የተላኩት ሰዎች፡ ቲቶ (16-17)፣ ስሙ ያልታወቀ ወንድም (18)፣ ሌላ ስሙ ያልተጠቀሰ ወንድም (22) ናቸው፡፡ ስጦታው የሚሰበሰብበትን ምክንያቶች በቁ20 ላይ ሲናገር የመጀመሪያውን ሥፍራ የሰጠው ‹‹ጌታን ራሱን ለማክበር›› ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ‹‹ሌሎችን ለመርዳት›› ነው ይላል፡፡
8. ስጦታችንን የሚያስተዳድሩ ሰዎች ባህርይና ብቃት መጠየቅ እንደምንችልና፤ መሪዎች ደግሞ መልስ የመስጠት ሃላፊነት እንዳለባቸው እንማራለን፡፡
9. ቲቶ ጳውሎስ ራሱ የሚመሰክርለት ሰው ነው (16-17፣ 23)፤ ሁለተኛው ወንድም በራሱ ቤተክርስትያን ብቻ ሳይሆን በአብያተ ክርስትያናት ሁሉ የተመሰከረለት ነው (18)፣ በተጨማሪም በአብያተ ክርስትያናት የተመረጠ ነው (19)፣ ሶስተኛው ወንድም ደግሞ በብዙ መንገድ ተፈትኖ የወጣለት ሰው ነው (22)፡፡ ይህንን የሚነግረን ጥቅስ ቁ20 ነው ብዬ አምናለሁ፡፡ ከዚህ መማር የምንችለው እግዚአብሄር የልቤን ያውቃል በሚለው መሸፈኛ ብቻ ልንመላለስ እንደማንችልና ከሰዎችም ሊወረወርብን ለሚችለው ነቀፋ ሁሉ ማሰብና አስፈላጊውን ሁሉ ጥንቃቄ ሁሉ ልናደርግ እንደሚገባን ነው፡፡

# ጥናት አስራ አንድ 2ኛ ቆሮ 9፡1-15 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ሌሎችን ለመርዳት እንደተዘጋጁ ለመቄዶንያ ሰዎች የተናገረ ሲሆን፤ በ2ኛ ቆሮ 8፡1 ደግሞ ለቆሮንቶስ ሰዎች  የመቄዶንያ ሰዎች ከእግዚአብሄር የተሰጣቸውን ጸጋ ምን ያህል እንደተጠቀሙበት ነው የተናገረው፡፡ ለአንዱ ስለሌላው መናገር የፈለገበት ምክንያት፣ አንዱ በሌላው እንዲበረታታና እንዲነቃቃ በማለት ነው (ቁ2ትን ማየት ይረዳል)፡፡
2. እነቲቶ የተላኩበት ምክንያት የቆሮንቶስ ሰዎች የገቡት ቃል ወሬ ብቻ ሆኖ እንዳይቀርና ለማድረግ ያሰቡትን በጎ ነገር በተግባር እንዲያውሉት ለማበረታታት ነው፡፡ ሰዎች ለጌታ የገቡትን ቃል ኪዳን መፈጸም እንዲችሉ በተለያየ መንገድ ማበረታታና መርዳት እንደሚኖርብን እንማራለን፡፡
3. በነዚህ ቁጥሮች መሰረት ወደ ቆሮንቶስ ሊደረጉ የታሰቡ ሁለት ጉዞዎች ሲሆኑ፤ የመጀመሪያው በቲቶ የሚመራ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በጳውሎስ የሚመራ ነው፡፡ በጉዞዎቹ ላይ ተሳታፊዎች የሚሆኑት ሰዎች፤ በምዕራፍ 8፡16-24 ያየናቸው ሶስት ሰዎች፣ በቁ4 ላይ እንደምናነበው ጳውሎስና ከመቄዶንያ ደግሞ ቁጥራቸው ያልታወቁ ሰዎች እንደሚሄዱ እናነባለን፡፡
4. በዚህ ቁጥር ላይ ሊያስታውሳቸው የሚሞክተው እውነት ሰው የዘራውን ያህል እንደሚያጭድ ነው፡፡ ይህ ጥቅስ የሚናገረው ስለዘሩ ብዛትና መጠን ሲሆን፤ በገላቲያ ላይ ያለው ጥቅስ ግን የሚናገረው ስለዘሩ ጥራትና ዓይነት ነው፡፡
5. ሁለት ዓይነት የመስጠት ዓይነቶች ሲኖሩ እነሱም በቅሬታና በግዴታ መስጠት አንዱ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ልባችን የፈቀደውን ያህል መስጠት ናቸው፡፡ ልንከተለው እንደሚገባን የተነገረን ሁለተኛውን የመስጠት ዓይነት ሲሆን፤ ምክንያት አድርጎ የነገረንም እግዚአብሄር በደስታ የሚሰጠውን መውደዱን ነው፡፡ ‹‹በልቡ ያሰበውን ያህል ይስጥ›› የሚለው በውስጡ ደስታን እንዳዘለ የሚነግረን፤ በዚያው በቁ7 ላይ እግዚአብሄር የሚቀበለውን ስጦታ አይነት ሲነግረን በደስታ የተሰጠ መሆኑ ይህንን ሃሳብ ይጠቁመናል፡፡
6. በቁ8 ላይ እንደሚሰጥ የተነገረው ነገር ‹‹ጸጋን›› ሲሆን፤ የሚሰጥበት ምክንያትም ‹‹ለበጎ ስራ ሁሉ እንድትተርፉ›› ነው ይላል፡፡ በቁ10 ላይ ደግሞ የምንበላውን እንጀራና የምንዘራውን ዘር ነው፡፡ ከነዚህ ጥቅሶች የምንማረው እግዚአብሄር ለራሳችን የምንበላውንና ለሌሎች የምንዘራውን መስጠት ብቻ ሳይሆን፤ የመስጠትን ተግባር ለመፈጸምም የሚያስችለንን ጸጋ ሁሉ የሚለግሰን እሱ እንደሆነ እንረዳለን፡፡
7. በዚህ ውስጥ የእነጳውሎስ ተሳትፎ ብዬ የማምነው የቆሮንቶስ ሰዎችን በእግዚአብሄር ቃል ማነቃቃት፣ ማስተማር፣ የገቡትን ቃል እንዳይረሱ ማሳሰብና፤ በሌላ በኩል ደግሞ እንደድልድይ በመሆን የተሰበሰበው ገንዘብ ለሚያስፈልጋቸው ሰዎች እንዲደርስ ማድረግ ነው፡፡ ከዚህ አገልግሎት የሚመጣው ውጤት በአንደኛ ደረጃ እግዚአብሄር ብዙ ምስጋና መምጣት ሲሆን፤ ሁለተኛ ደግሞ የቅዱሳንን ጉድለት ያሟላል፡፡
8. በዚህ ክፍል እንደ ክርስቶስ ወንጌል ተደርጎ የተነገረለት ነገር ለሌሎች የምናሳየው ልግስና ነው፡፡ ለልግስና አገልግሎት ትልቅ ስፍራ የተሰጠው ነገር የእግዚአብሄር ጸጋ ነው፡፡

# ጥናት አስራ ሁለት 2ኛ ቆሮ 10፡1-18 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በሰው ፊት ሲሆን ዓይነ አፋር፣ ከሰዎች ርቆ ሲገኝ ግን ደፋር አድርገው የቆሮንቶስ ሰዎች እንደሚያዩትና እንደሚናገሩ ነው፡፡ በአለማዊ መንገድ እንደሚኖር አድርገው የሚቆጥሩትና፤ ሌሎች ከዚያ በተለየ መንገድ የሚያዩት የተለያዩ ሰዎች እንዳሉ ነው የሚናገረው፡፡
2. መንፈሳዊ ውግያ ከሥጋዊ ውግያ የሚለይባቸው ሁለት ነገሮች፤ በውግያ ስልት ይለያያሉ (ቁ3)፣ ሌላ ደግሞ በጦር መሳሪያ ይለያያሉ (ቁ4)፡፡ የእኛ የጦር መሳሪያ ምሽግን ለመደምሰስ የሚችል መለኮታዊ ሃይል እንዳለው ያረጋግጥልናል፡፡
3. የጦር መሳሪያችን ሃይል ያለው ለማፍረስና እንዲሁም ለመገንባትም ጭምር ነው፤ በቁ5 ላይ ስናነብ ለማፍረስ የሚችልበትን ሃይል ‹‹እናፈርሳለን›› ከሚለው አነጋገር ስናይ፤ የመገንባት ችሎታውን ደግም በዚያው ቁጥር ውስጥ ‹‹ለክርስቶስ እንዲታዘዝ እናደርጋለን›› ከሚለው ሃሳብ እናገኛለን፡፡ ቀጣይ ፕሮጀክት አድርገው የያዙት እንቢተኞቹንና የሃሰት አስተማሪዎችን በዚህ መለኮታዊ ሃይል የለመቅጣት ዘመቻ ነው፡፡
4. ጳውሎስ ሥልጣን እንዳለው ያውቃል፣ ሥልጣኑን ከጌታ እንደተቀበለ፣ በተቀበለው ሥልጣንም ትምክህት፤ ሥልጣኑ የተቀበለበት ምክንያት መረዳቱ፤ ያም ቅዱሳንን ለማነጽ እንጂ ለማፍረስና ተስፋ ለማስቆረጥ እንዳልሆነም ተረድቷል፡፡
5. አንዳንዶች ቁ10 እንደሚናገረው የጳውሎስ መልእክቱ ከባድና ጠንካራ እንደሆነና በስጋ ፊት ለፊት ሲታይ ግን ደካማና ንግግሩም የተናቀ መሆኑን እንደሚናገሩ ያውቃል፡፡ ለዚህ አመለካከት የጳውሎስ ምላሽ በቃል የሚናገረውን ነገር በተግባር የሚተረጉም ሰው፣ ማለትም ቃሉና ሥራው እንደማይለያይ ነው፡፡ ቃላችንና ኑሯችን አንድ መሆን እንደሚኖርበት መማር እንችላለን፡፡
6. ጳውሎስ ከማድረግ የተቆጠበው ነገር ራሳቸውን ከሚያመሰግኑ ሰዎች ጋራ ራሱን ማነጻጸር ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች የሚያደርጉት ራሳቸውን በራሳቸው መመዘንና፣ ራሳቸውን ከራሳቸው ጋራ ማነጻጸር ነው፡፡ ስምርናም ሆነ ሎዶቅያ ራሳቸውን ያዩበት ጌታ ከሚያያቸው የተለየ መሆኑ፤ ጌታ የሚነግረንን እንጂ ስለራሳችን የምናስበው ልክ ላይሆን እንደሚችል እንረዳለን፡፡
7. ጳውሎስ ራሱን ከሌሎች ሰዎች ጋራ ራሱን ማወዳደር ትቶ እግዚአብሄር ለእርሱ በመደበለትና በወሰነው ነገር ላይ በማተኮር ላይ እንዳለ ነው የሚናገረው፡፡ ለጳውሎስ እግዚአብሄር የመደበለት የአገልግሎት ድርሻ ምንም እንኳን ወንጌልን ለፍጥረት ሁሉ ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ ቢናገርም፤ በተለይ ለአህዛብ ሃላፊነትን እንደተቀበለ ከእነዚህ ጥቅሶችና ከሌሎችም እንረዳለን፡፡
8. ይህ በቁ18 ላይ የምናየው ሃሳብ በእግዚአብሄር ፊት ተቀባይነት የሚገኘው እግዚአብሄር ራሱ ሲያመሰግነን እንጂ ራሳችንን ስናመሰግን እንዳልሆነ ሲናገር፤ ቁ12ትም በሌላ አነጋገር ራስን ማመስገን ሞኝነት ወይም ራስን ማታለል እንደሆነ አድርጎ ነው የሚናገረው፡፡
9. ጳውሎስ እያደረገ ያለው ነገርና ጥረቱ ወንጌል ላልደረሳቸው ሰዎች ሁሉ እንዲደርስ ሌሎች ሰዎች ወንጌልን በተናገሩበት ስፍራ ሳይሆን ሁልጊዜ ለወንጌል አዲስ የሆነ ሥፍራ ላይ የሚያተኩር ሲሆን፤ በእኛ ዘመን ሁኔታው የተገላበጠ ይመስላል፤ ምክንያቱም ባብዛኛው የወንጌል አገልጋዮች ክምችት ሲታይ ምቾት ባለባቸው  ከተሞች አካባቢ ሲሆን ይህም ግጭትና አለመስማማትን ፈጥሮ ለወንጌል የባሰ እንቅፋት ሆኗል፡፡

# <u>ጥናት አስራ ሶስት 2ኛ ቆሮ 11፡1-15 (ለመሪው የተዘጋጀ)</u>

1. ጳውሎስ ሰዎቹን ለራሱ እያዘጋጃቸው እንደሆነ የሚያሳየን በቁ2 ላይ የምናነበው ሃሳብ ሲሆን፤ ይህም እንደሙሽራ ለክርስቶስ ሊያቀርባቸው እንደሆነ ይነግረናል፡፡ የጳውሎስ ስጋቱ እነዚህ ለክርስቶስ ያጫቸው ሰዎች እንዳይስቱና የውስጣቸው ተበላሽቶ ካላቸው ቅንነትና ንጽህና እንዳይወሰዱ ነው፡፡
2. በዚህ ሥፍራ ጳውሎስ እነዚህን ሰዎች የሚመስላቸው ሄዋንን በተንኮል ባሳተው በእባብ ሲሆን፤ ከዚህም አባባሉ ተንኮልና ክፋትን የተሞሉ እንደሆኑ መረዳት እንችላለን፡፡ አንድ ሚስት ለአንድ ባል መሆኑን፣ ከዚህ በኋላ ወደ ሌላ መከጀል እንደሌለና ባልና ሚስት እርስ በእርስ አንዳቸው ለሌላቸው በመሰጠት መኖርን የሚያመለክት ሲሆን፤ በክርስቶስና በአማኝ መሃል የሚኖረውም ግንኙነት ይህንኑ ማንጸባረቅ እንደሚኖርበት ነው፡፡
3. እነዚህ ተንኮለኞች የሚጠቀሙባቸው የመሳሪያ አይነቶች፤ ሌላ ኢየሱስ፣ የተለየ መንፈስና፣ የተለየ ወንጌል ናቸው፡፡ በዘመናችንም እነዚህ ልዩ ወንጌል፣ ሌላ ኢየሱስና ልዩ መንፈስ ከሌሎች ዘመናት እንዲያውም በበለጠ የሰይጣን መሳሪያ እንደሆኑ ለመረዳት አያዳግትም፡፡
4. አገልግሎቱን ከሌሎች ያነሰ አድርገው እንዲያዩት ዋነኛ ምክንያት አድርጎ የሚናገረው ነገር፤ ጳውሎስ ወንጌልን ምንም ከእነሱ ገንዘብ ሳይፈልግ በነጻ ስላገለገላቸው፤ በእነርሱ አመለካከት እውነተኛ አገልጋይና ሃዋርያ ቢሆን እንደሌሎቹ ሁሉ ገንዘብ መቀበል ነበረበት የሚለው አመለካከት ነው፡፡ በነጻ ወይም በገንዘብ ላይ ሳያተኩር ወንጌልን ለሚያስተምር ሰው ከቆሮንቶስ የተለየ አመለካከት አለኝ፤ ይኸውም ያንን ማድረጉ የበለጠ ልቡ በገንዘብ ላይ እንዳልሆነ ማረጋገጫ ይሰጠኛል ብዬ አምናለሁ፡፡
5. ምክንያት አድርጎ የሚያቀርበው ነገር ክርስትያኖች የስንፍናን ህይወት እንዳይለማመዱ የህይወት ምሳሌ መሆንና፤ በሰዎች ላይ ሸክም አለመሆን የሚሉት ናቸው፡፡ በተለይ የተሰሎንቄውን ጥቅስ ስናይ ‹‹የሚያስፈልገንን ከእናንተ ለማግኘት ስልጣን ሳይኖረን ቀርቶ አይደለም›› የሚለው አነጋገር ከእነርሱ ገንዘብ የመቀበል መብት እንደነበረው ያስረዳናል፡፡ ከዚህ መማር የምንችለው ነገር፤ ሰዎችን ከምንሰብካቸው በተጨማሪ በህይወታችን የምናሳያቸው ምሳሌነት ለለውጣቸው ትልቅ ስፍራ ሊኖረው እንደሚገባ እማራለሁ፡፡
6. እነዚህ ሰዎች በ2ኛ ቆሮ 10፡17 ከሚገኘው ሃሳብ ጋራ ህይወታቸው የሚቃረንበት መንገድ፤ ያ ክፍል የሚያስተምረን የሚመካ ማንም ሰው በጌታ እንዲመካ ሲሆን፤ እነሱ ግን የሚመኩት በራሳቸው ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች ከነጳውሎስ ጋራ ሊወዳደሩ እንዳይችሉና እኛም እንደነሱ ነን ማለት እንዳይችሉ ጳውሎስ እያደረገ ያለው ነገር ወንጌልን ያለዋጋ በነጻ ማስተማር ነው፡፡
7. እነዚህን ሰዎች የሚጠራቸው፤ ራሳቸውን የሚለዋውጡ፣ ሐሰተኞች ሃዋርያትና፣ አታላዮች ሰራተኞች ይላቸዋል፡፡ ሶስት ጊዜ ተደጋግሞ የተነገረው ዓረፍተ ነገር ‹‹ለመምሰል ራሳቸውን ይለውጣሉ›› የሚለው ሃሳብ ሲሆን ቁ13፣ ቁ14፣ እና ቁ15 ላይ ይገኛል፡፡
8. የሰይጣን አገልጋዮችና፣ የጽድቅ አገልጋዮች ብሎ የሚጠራቸው ናቸው፡፡ የሰይጣን አገልጋዮች ዋነኛ ባህርይ ሆኖ የማየው ሌላውን ለመምሰል መሞከር ማለትም ራስን ሆኖ ያመገኘት ባህርይ ነው፡፡ የሰውን አሰባበክ፣ አዘማመርና የመሳሰሉትን መንፈስ ቅዱስ ለራሳችን የሰጠንን ትተን ሌላውን ለመምሰል የምንሞክረው ችግር አይበታለሁ፣ ሆኖም በቅድስና መልካም የህይወት ምሳሌ እያንጸባረቁ የሚኖሩትን መምሰል ግን ቃሉ ራሱ የሚያበረታታን ስለሆነ መልካም ነው ብዬ አምናለሁ፡፡

# ጥናት አስራ አራት 2ኛ ቆሮ 11፡16-33 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ስለራስ መናገርና ትምክህት ከጳውሎስ ሊማሩ የሚያስፈልጋቸው ነገር እንዳልሆነና ሊከተሉ የሚገባቸው ምሳሌነት እንዳልሆነ የተናገረ የሚመስለኝ በቁ17 ላይ ‹‹እንደዚህ ልበ ሙሉ ሆኜ የምናገረው እንደ ሞኝ እንጂ እንደ ጌታ ፈቃድ አይደለም፡፡›› የሚለው አነጋገሩ ግልጽ ያደርገዋል፡፡
2. የቆሮንቶስ አማኞች በማይገባ ሁኔታ እነዚህን ሰዎች እየታገሱ ያሉት፡ ባሪያ ያደርጓቸዋል፣ ይበዘብዟቸዋል፣ ለጥቅማቸው ሲሉ ይጠጓቸዋል፣ ይንቀባረሩባቸዋል፣ ፊታቸውን በጥፊ ይመቷቸዋል፡፡ ጳውሎስ ይህንን አነጋገር ሲናገር የዚህ ዓይነቱን አለማድረጋቸው በቆሮንቶስ ሰዎች ፊት ደካማ ሊያሰኛቸው የሚችል ነገር እንደሆነ ቢያውቁም፤ በእግዚአብሄር ፊት ሃጥያት ስለሆነ ሊያደርጉት ፈቃደኞች አለመሆናቸውን የሚጠቁም ነው፡፡
3. ‹‹እነረሱ›› እያለ የሚጠራቸው በቆሮንቶስ ቤተ ክርስትያን ህዝቡን እያሳቱና በነጳውሎስ ላይ እያነሳሱ ያሉትን ሰዎች ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች እየተመኩ ያሉባቸው ነገሮች በቁ22 ላይ እንደሚታየው በእብራዊነታቸው፣ በእስራኤላዊነታቸው፣ በአብርሃም ልጅነታቸውና፣ በክርስቶስ አገልጋይነታቸው ነው፡፡
4. ጳውሎስ እንደ ቀውስ ሆኖ እንዲናገር የገፋፋው ነገር የእነዚህ ሰዎች የክርስቶስ አገልጋይ ነኝ በማለት የሚፎክሩት ፉከራና የሚያሳዩት ትምክህት ነው፡፡ ይህንን ዓይነት አነጋገር እኛ ዛሬ በሌሎች ላይ ተነስተን እኔ እበልጥሃለሁ እያልን ልንፎክር የተተወልን ምሳሌነት አይደለም፤ ምክንያቱም በቁ17 ላይ እንደተመለከትነው ይህ እያደረገ ያለው ነገር የጌታ ፈቃድ እንዳልሆነ በግልጽ ነግሮናልና ነው፡፡
5. ለዚህ ጥያቄ መልስ እንዲሆን በቁ23-27 የተዘረዘሩትን ነገሮች ሁሉ ማስፈር ይቻላል፡፡ በዘመናችን የክርስቶስ አገልጋይ የሚለው ሃሳብ በብዙ አገልጋዮች አመለካከት የእግዚአብሄር አምባሳደር ከመሆኑ የተነሳ ከማንም ሰው የተሻለ ኑሮ፣ ምቾትና ድሎት ሊሰጠው እንደሚገባ ይነገራል፤ ከጳውሎስ አነጋገር እንደምንረዳው ግን የክርስቶስ አገልጋይ ማናቸውንም ዓይነት ምድራዊ መከራ ለተሰጠው አደራ ሲል ሊሸከም ፈቃደኛ እንደሆነ እናያለን፡፡
6. ጳውሎስ ይህንን ሁሉ መከራና ችግር ሲሰነዝር የክርስቶስ አገልጋዮች ሁሉ ይህንን መቅመስና መለማመድ ይኖርባቸዋል በሚል እምነት አይመስለኝም፣ ነገር ግን የክርስቶስ አገልጋይ ለተቀበለው የወንጌል አደራ አስፈላጊውን መስዋዕትነት ሁሉ ለመክፈል ፈቃደኛ ሊሆን እንደሚገባው ለማስተማር ይመስለኛል፡፡
7. ጳውሎስ የመከራና የስቃዩን ብዛት ከመናገር ይልቅ የመሰረታቸውን አብያተክርስትያናት ቁጥር፣ በእርሱ አማካኝነት የዳኑትን ነፍሳት ብዛት፣ ጌታን ለማገልገል የተጓዘውን ርቀት፣ ያፈራቸውን ደቀመዛሙርት ቁጥርና፣ በእጁ የተፈወሱትን ሰዎች ብዛትና የመሳሰሉትን ሁሉ በመደርደር አፋቸውን ማዘጋት ይችል ነበረ፡፡ ጳውሎስ ከላይ ደረሰብኝ ብሎ የዘረዘራቸው ነገሮች በማጋነን እንዳልተነገሩና ሁሉም እውነት መሆኑን ለማረጋገጥ ነው፡፡
8. ጳውሎስ እውነተኛ የክርስቶስ አገልጋይ እንደሆነ የሚያረጋግጥልን ሃሳብ፤ በእርሱ ህይወት ላይ ይህ ሁሉ መከራና ስደት እየወረደበት እርሱ ግን እለት በእለት የሚያስጨንቀው የራሱ ሁኔታ ሳይሆን በየስፍራው ያሉት ቅዱሳን ነገር መሆኑ ነው፤ ይህም ማለት በቁ29 ላይ እንደሚነግረን የሌሎችን ድካም የእርሱ ድካም እንደሆነ እየቆጠረ፣ የሌሎች መሰናከልም ደግሞ እንደራሱ መሰናከል አድርጎ የሚያይ ሰው መሆኑ እውነትም ራሱን የካደ የክርስቶስ አገልጋይ ማለት እንችላለን፡፡

## ጥናት አስራ አምስት 2ኛ ቆሮ 12፡1-21 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. እስከ ሶስተኛው ሰማይ ድረስ የተነጠቀበትን በሰው አንደበት ሊገለጥ የማይችልና ሰውም እንዲናገረው ያልተፈቀደለትን ነገር ስለመስማቱ ነው፡፡ ይህንን ልምምዱን መናገሩ ሞኝ ሊያሰኘው የማይችልበት ምክንያት ቁ6 ላይ እንደሚነግረን የሚናገረው ነገር እውነት ስለሆነ ነው፡፡
2. እርሱ ያየውን መገለጥ ‹‹ታላቅ መገለጥ›› በማለት ነው የሚናገረው፡፡ መጠንቀቅ የሚያስፈልገን ምክንያት ትዕቢት ወደ ህይወታችን ሊገባ ስለሚችል ነው፡፡ በዚህ ቁጥር ላይ የሚታየው ስጦታ ከፉ መስሎ ቢታይም ነገር ግን በጳውሎስ ህይወት ውስጥ የሚያስገኘው ውጤት መልካም ነው፤ ስለዚህም ማቴ 7፡11 ከሚናገረው ሃሳብ ጋራ ያለምንም ችግር ይዛመዳል ብዬ አምናለሁ፡፡
3. በጳውሎስ አመለካከት ይህ የእግዚአብሄር ስጦታ አይጠቅመውም፣ አያስፈልገውም፤ በእግዚአብሄር አመለካከት ሲታይ ደግሞ ይህ ስጦታ ለጳውሎስ ህይወት አስፈላጊ ሆኖ ያየዋል፡፡ በ1ኛ ዮሐ 5፡14 ‹‹ማንኛውንም ነገር እንደ ፈቃዱ ብንለምን እርሱ ይሰማናል፡፡›› የሚለው ሃሳብ በሁለቱ መሃል የሚታየውን ክፍተት በሚገባ ይደፍነዋል እላለሁ፡፡
4. እነዚህ ሁለት አነጋገሮች የሚቃረኑ ሃሳቦች አይደሉም ምክንያቱም፤ በቁ6 ላይ እየተናገረ ያለው ትምክህት ካስፈለገና ብመካም ሞኝነት የማይሆንበት ምክንያት የጉራና ውሸት ነገር የምናገር ሳይሆን የሆነ ነገር ስለምናገር እውነት ነው፤ በቁ11 ላይ ግን ይህንን እግዚአብሄር በህይወቴ የሰራውን ነገር ቁ6 እንደሚለው በሰዎች ዘንድ ከሆነው በላይ ከፍ ተደርጎ እንዲታይ ስለሚያደርገው ተገፍቶ ያደረገው ነገር መሆኑን ለማሳየት ነው፡፡ የቆሮንቶስ እርሱ ትምክህት ውስጥ እንዳይገባ ከእነርሱ ጋራ ብዙ ጊዜ ስላጠፉ ስለእርሱ ማንነት ያዩትን በመናገር ሊረዱት ይችሉ ነበረ፡፡
5. የሚያወዳድራቸው ሁለት ነገሮች፤ የመጀመሪያው ራሱን ከሌሎች ሐዋርያት ጋራ ማለትም የቤተ ክርስትያን አገልጋዮችን ሲያወዳድር፣ በሌላ በኩል ደግሞ የቆሮንቶስን ቤተ ክርስትያን ከሌሎች አብያተ ክርስትያናት ጋራ በማወዳደር ይናገራል፡፡ በእርሱ አመለካከት እንደቤተ ክርስትያን ቆሮንቶስ ከየትኛውም ቤተ ክርስትያን እንደማታንስና አገልጋያቸውም ጳውሎስ ሐዋርያት ከተባሉት ከማናቸውም እንደማያንስ ያረጋግጥላቸዋል፡፡
6. በዚህ ክፍል ላይ ጳውሎስ ራሱን እንደ ወላጅ አድርጎ ነው የሚያቀርብላቸው፡፡ 1) ከተገልጋዮቹ ሊያገኝ የሚችለውን ነገር ሳይሆን እነርሱን ራሳቸውን የሚፈልግ መሆኑ ይታያል፡፡ 2) ራሱን እንደ ወላጅ በመቁጠር በመስጠት ላይ እንጂ በመቀበል ላይ ያተኮረ አገልግሎት አልነበረውም፡፡ 3) የፍቅሩ መጠን ለሚያገለግላቸው ሰዎች ያለውን ነገር ብቻ ሳይሆን ራሱንም እንኳን ለመስጠት የተዘጋጀ አገልጋይ ነው፡፡
7. ቲቶና ጳውሎስ ከቆሮንቶስ ቤተ ክርስትያን ገንዘብ አለመቀበልን የመረጡበት ምክንያት በቁ19 እንደሚናገረው ‹‹ይህን ሁሉ የምናደርገው እናንተን ለማነጽ ነው፡፡›› ይላል፡፡ ጳውሎስ ቆሮንቶስን ስለመጎብኘት ሲያስብ የነበሩት ፍርሃቶች ቁ20 እርሱ እንደሚፈልጋቸው ሆነው ላይገኙ ይችላሉ፤ ወይም እነርሱ እንደሚፈልጉት ሆኖ ላይገኝ ይችላል ብሎ ይፈራል፤ ሁለተኛው ደግሞ በቁ20 ላይ የዘረዘራቸው ሃጥያቶች ይኖራሉ ብሎ ይሰጋል፤ በሶስተኛ ደረጃ ደግሞ በቀድሞ ሃጥያታቸው ንስሃ ያልገቡ ሰዎች ይኖራሉ ብሎ ይፈራል (ቁ21)፡፡
8. በዚህ ቁጥር ላይ ከምናየው ጳውሎስ ስለራሱ መመካት ያልፈለገበት ምክንያት ሰዎች ስለእርሱ ከሚያዩትና ከሚሰሙት በላይ ከፍ አድርገው እንዳይገምቱት በሚያደርገው ጥንቃቄ ነው፡፡

# ጥናት አስራ ስድስት 2ኛ ቆሮ 13፡1-14 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በተደጋጋሚ ማስጠንቀቂያ መስጠት ያስፈለገበት ምክንያት ቁ3 ላይ እንደምናነበው ክርስቶስ በነጳውሎስ ውስጥ ሆኖ እንደሚናገር በመጠራጠራቸውና ማስረጃ በመፈለጋቸው ነው፡፡
2. ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሆኖ ሳለ የእግዚአብሄር ልጅስ ከሆንክ ራስህን አድን ተብሎ ራሱን ማዳን እንኳን እንደማይችል እንዳሾፉበት.፤ በሶስተኛው ቀን ግን ድል አድርጎ በሃይል እንደተነሳ ታይቷል፡፡ እንደዚሁም ደግሞ እነጳውሎስ ለጊዜው በሃጥያት እየኖሩ ያሉትን ሳይቀጡ የመምከርና የማስተማርን መንገድ ብቻ መከተል በሰዎች ዓይን ደካማነት ሆኖ ቢታይም፤ አስፈላጊው ጊዜ ሲመጣ የክርስቶስ ሃይል በእነርሱ ውስጥ እንደሚገለጥና በሃጥያት ለሚመላለሱትም እንደማይራሩላቸው በግልጽ ተናገሯል፡፡
3. ፈተናውን ተፈትኖ ባለፈና በወደቀ መሃል የሚኖረው ልዩነት፤ ተፈትኖ ያለፈው ሰው ኢየሱስ ክርስቶስ በውስጡ ያለ ሲሆን፤ ተፈትኖ የወደቀ ሰው ግን ክርስቶስ በውስጡ የማይኖር ሰው ነው፡፡ ይህንን ሚዛን የምናይበት ሌላው የመጽሃፍ ቅዱስ ክፍል ሮሜ 8፡9ን ነው፡፡ ጳውሎስና ከእርሱ ጋራ የሚያገለግሉት ጓደኞቹ ፈተናውን ተፈትነው ያለፉ ሰዎች እንደሆኑም በቁ6 ላይ ይናገራል፡፡
4. ለቆሮንቶስ ሰዎች እነጳውሎስ ይጸልዩበት የነበረው የጸሎት ርዕስ፡ እነዚህ ሰዎች ምንም ዓይነት ክፉ ነገር እንዳያደርጉ ነው፡፡ ጸሎታቸው ግለኝነት እንደሌለበት የተናገረው እኔ እንደገባኝ ከሆነ ስለእነጳውሎስ በተቃውሞ እየተነገረ ያለውና ሰዎች እነሱ ብቁዎች እንዳልሆኑ የሚናገሩት እንዲቆም ካላቸው ፍላጎት የመነጨ ሳይሆን በቅዱሳኑ ህይወት ማደግ ላይ የተመሰረተ እንደሆነ ሲናገር ነው፡፡
5. በዚህ ቁጥር ላይ እነጳውሎስ ከጌታ የተቀበሉት መንፈሳዊ ሥልጣን እንደሆነ እመለከታለሁ፡፡ ይህንን ስልጣን መጠቀም የሚችሉባቸው ሁለት መንገዶች ይታዩኛል፡፡ ከነዚህም መንገዶች የመጀመሪያው ሥልጣናቸውን በሃይል ለቅጣትና ለማረም መጠቀም ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ ለማነጽና ለመገንባት መጠቀም ነው፡፡ እነርሱ የመረጡት ሁለተኛውን፣ ማለትም ቅዱሳንን ለማነጽ እንደሆነ ክፍሉ ያረጋግጥልናል፡፡
6. ቁ10 እነጳውሎስ ከጌታ ሥልጣን የተቀበሉ ሰዎች እንደሆኑ ቢያውቁም ሥልጣናቸውን ለማሳየት መቼ ሁኔታው ተፈጥሮልን በማለት የሚጠባበቁ ሰዎች እንዳልሆኑ ነገር ግን፤ ቁ9 እንደሚለው እነርሱ እንደ ደካሞችና ሥልጣን እንደሌላቸው ተቆጥረው በአንጻሩ የቆሮንቶስ ቅዱሳን በህይወታቸው ወደ ክርስቶስ ወዳሰበላቸው ወደ ሙላቱ አድገው፣ ብርቱ አማኞች መሆናቸው የእነጳውሎስ ጸሎትና መሻት እንደሆነ እንረዳለን፡፡
7. እነዚህን ሰዎች በቁ11 ላይ ‹‹ወንድሞች›› እያለ ነው የሚጠራቸው፡፡ ጳውሎስ የቆሮንቶስን ሰዎች ከጌታ የተቀበለውን ሥልጣን ያልተቀበሉና እንፈልግህም የሚሉትን ሰዎች ‹‹ወንድሞች›› እያለ መጥራቱ፤ ሰዎች ስለእኛ ምንም ዓይነት አመለካከት ቢኖራቸውና ከእኛ ጋራ አለመስማማታቸውን ቢገልጹም ወንድምና እህትነታቸውን እንደማይለውጠው የሚያስተምረን ነው፡፡
8. የቆሮንቶስ ሰዎች እየጠየቁ ያሉት ነገር ክርስቶስ በጳውሎስ ውስጥ አለ ወይ? በጳውሎስ ውስጥ የሚሰራው ክርስቶስ ነው ወይ የሚሉትን በጳውሎስ ላይ ያተኮሩ ጥያቄዎች ሲሆን፤ ጳውሎስ ግን ‹‹እኔ ራሴ በክርስቶስ ውስጥ ነው ወይ ያለሁት?›› የሚለውን ጥያቄ ራሳቸውን እንዲጠይቁ ነው እነዚህን ሰዎች የሚመክረው፡፡